# <u>መከራው ይቀጥል</u>

<u>ሚያዝያ 22 ቀን 2013 ዓ/ምህረት</u>

ቀሲስ አስተርአየ nigatuasteraye@gmail.com

“እንበለ ደዌ ወህማም፡ እንበለ ጻማ ወድካም፡ ያብጽሀነ

ያብጽሀክሙ ዓመ ከመ ዮም በፍሥሐ ወበሰላም”

ከዚህ በላይ የሰፈረው አረፍተ ነገር በሰሙነ ህማማቱ ለሚደረገው የዓመታዊው ስርአተ ጸሎት መዝጊያ ነው። ጽንሰ ሀሳቡ ህማማቱ በሚታሰብበት ዓመት ህዝቡ በሰላም በመረጋጋት በጤና ያስታወሰው መሆኑንና የሚቀጥለውንም ህማማት በተመሳሳይ መረጋጋት እንዲያስታውሰው ምኞትን የሚያንጸባርቅ ነው።

አረፍት ነገሩ ቃል በቃል ሲተረጎም፡-“ <u>ያለበሽታና ያለደዌ ፤ ያለ ድካምና ያለጻእር፤ የዘንድሮውን ሰሙነ ህማማት በደስታ በሰላም እንዳከበርነው፤ የከርሞውንም በተመሳሳዩ ለማክበር ያብቃን“</u> ማለት ነው። ታዲያ የዘንድሮውን ህማማት ያለበሽታና ያለደዌ ፤ ያለ ድካምና ያለጻእር፤ በደስታ በሰላም ነበር ያስታወስነው? በዚህ ዓመት ያለንበት ሁኔታ እንዳለ ቀጥሎ የከርሞውንም ህማማት በተመሳሳይ ችግርና መከራ እንድናስታውሰው የሚያስመኝ ነው?ጠላት ካልሆነ በቀር የዘንድሮው መከራና ስቃይ በሚቀጥለው ዓመት በህብረተ ሰብ ላይ እንዲደገም የሚመኝ ይኖራል ተብሎ የሚታሰብ ሰው የለም።

በህማማቱ ሰሞን የሚነበቡት በክርስቶስ ላይ የሚታወሰውን መከራ ጸሐይና ጨረቃ ሳይቀሩ ገጻቸው መለወጣቸውን እመቤታችን በመረረ ሀዘን ውስጥ መሆኗንና ሐዋርያትም በሞት ጥላ ስር መውደቃቸውን የሚያሳዩ ናቸው። ከክርስቶስ ሰቃዮችና ገዳዮች በቀር ከክርስቶስ ጋራ ቀረቤታ የነበራቸው ሁሉ በፍስሀ በደስታ ላይ አልነበሩም። “የዘንድሮውን ሰሙነ ህማማት ያለበሽታና ያለደዌ ፤ ያለ ድካምና ያለጻእር፤ በደስታ በሰላም እንዳሰብነው ፤ የከርሞውንም በተመሳሳዩ ለማሰብ ያብቃን“ ማለት፡- በክርስቶስ ላይ የተፈጸመው ጸዋተወ መከራ ውሸት ነበር። ወይም መከራውና ስቃዩ አሁንም ይቀጥል ማለት ነው።

አባባሉ ኢየሱስ ክርስቶስን ግረፈው እያሉ ካስገረፉት፡ስቀለው እያሉ ካሰቀሉት ሰዎች እጅግ በጣም የባሰ ጨካኝ የሚያስመስል ነው።

ታዲያ እስከ ቅዳም ስእርት ድረስ በሰሙነ ህማማት ለጸሎቱ መደምደሚያ "እንበለ ደዌ ወህማም፡ እንበለ ጻማ ወድካም፡ ያብጽሀነ ያብጽሀክሙ ዓመ ከመ ዮም በፍሥሐ ወበሰላም" የሚለውን፡- ያለምንም መሰቀቅ እየደጋገሙ የዘንድሮውን ሰሙነ ህማማቱን ያስታወሱ ሰዎች በኢትዮጵያ ያሉ ኢትዮጵያውያን ናቸው ብሎ መቀበል ይቻላልን? በዘንድሮው ሰሙነ ህማማት ላይ ተደርቦ የተከሰተው ሁሉ መከራ አንዷት ሳትጎድል ከርሞም ይደገም ከማለት የከፋ ምን በደልና ጥላቻ ይኖራል? በኦነግ ሸኔ በወያኔወችና ይህን እያልን የዘንድሮውን ህማማት ባስታወስነው ካህናት መካከል ምንልዩነት አለ?

አባባሉ ከገደያዮች ስሜትና ምኞት ጋራ የሚስማማ፤ ክርስቶስን ማስወገድ ይገባን ስለነበረ አስወገድነው። የህዝብ ጠላት ነበረና ተመልሶ እንዳይመጣ በማድረግ መልካም ተልእኳችን ፈጸምን። ለከርሞም ክርስቶስን የመሰለ ሰው ቢከሰት ክርስቶስን ባስወገድንበት ጀብዱ ለማስወገድ ያብቃን ማለት ነው።

ይህ ዓመታዊ ብሂል በግእዙ ለህዝቡ ሲነገር የሰነበተው ማህበራዊ ሁኔታ ሳይናጋ በደስታና በሀሴት የሚያስታውስበትን ዘመን የሚያንጸባርቅ እንጅ ይህን በመሰለ ክፉ ዘመን እንደወረደ ሊባል የሚገባው አልነበረም። ብዙ ነገሮችን ያስተማሩን ሊቃውንት በገጠሟቸው ክፉ ዘመናት በግራኝ መሀመድ በአድዋ በነ አጼ ሱስንዮስ ባምስቱ ወረራ ዘመናት ሰሙነ ህማማቱን " "የዘንድሮውን ሰሙነ ህማማት ያለበሽታና ያለደዌ ፤ ያለ ድካምና ያለጻእር፤ በደስታ በሰላም እንዳከበርነው፤ የከርሞውንም በተመሳሳዩ ለማክበር ያብቃን" የሚለውን እንደወረደ እየተናገሩት አሳለፉት ማለት ፈጽሞ አይገመትም።

ይህች ብሂል ተጽፈው በሚነበቡት መካከል ተመዝግባ ባትነበብም፤ "በመጽሐፍ ያለ ይወረሳል በቃል ያለ ይረሳል" እንደሚባለው፡- ቅዱስ ጳውሎስም "በቃላችንም ቢሆን" እንዳለው ፤ በቃላት ቅብብሎሽ ከትውልድ ወደትውልድ እየተሻገሩ ከኛ ከደረሱት ብዙ ነገሮች አንዷ ናት።

አባቶቻችን በገጠሟቸው የመከራ ዘመናት ያስታወሷቸውን ሰሙነ ህማማት እንዴትና ምን እያሉ አስታውሰዋቸው አለፉ የሚል ጥያቄ በጉባዔ ቤቶች ሳይነሳ የሚቀር የለምና ተነስቷል። መምህራን የሰጡት መልስ "ከመ ዮም" የምትለው ቃል በዘመነ ፍስሐና በዘመነ መንሱት መካከ ለሚከሰቱት ንጽጽር ስለሆነች ተመዛ መውጣት ነበረባትና በመከራና በስቃይ ዘመን ሊቃውንት አበው እየመዘዙ ያወጧታል " ይላሉ።

በመከራ ዘመን ህማማቱን የሚያስታውሱ ሁሉ ካህናት ከህዝብ የተለዩ ባእዳን፤ ወይም ያልገባቸው <u>ካልሆኑ፤ መቼም በዘመነ ሰላምና በዘመነ ሐሴት ለሚታሰበው ህማማት የሚባለውን</u> <u>"የዘንድሮውን ሰሙነ ህማማት ያለበሽታና ያለደዌ ፤ ያለ ድካምና ያለጻእር፤ በደስታ በሰላም እንዳከበርነው፤ የከርሞውንም በተመሳሳዩ ለማክበር ያብቃን"</u> ይላሉ ተብለው አይገመቱም።

በመከራ በስደትና በሀዘን በስቃይ ላይ ሳሉ ይህን የሚሉ ካሉ፤ ወይ ቋንቋ ያልገባቸው ወይም የህዝቡ መከራ ያልደረሰባቸው ወይ በህዝቡ ላይ ይህ ሁሉ መከራና ስቃይ እንኳን ደረሰበት ብለው የረኩ የህዝብ ጠላቶች መሆን አለባቸው ይላሉ።

ምንም እንኳ በዚህ ሶስት አመታት የተፈጸመው የከፋ ቢሆንም፤ ወያኔወች ኦርቶዶክሱንና አማራውን ሰበርነው እያሉ ባዋጅ እትዮጵያን ከተቆጣጠሩበት ቀን ጀምሮ በኢትዮጵያ ምድር <u>**አራት ማንነቶችን**</u> ይዘው በተገኙ ዜጎች ላይ እያደረሱት ያሉት የመከራና የስቃይ አይነቶች በጠላት ላይ አይድረሱ፤ እንደገና አያጋጥሙን የሚያሰኙ ናቸው። <u>**አራቱ ማንነቶች**</u> ከዚህ በታች የተገለጹ ናቸው።

1ኛ፡-ሰውነት

2ኛ፡-ኢትዮጵያዊነት

3ኛ፡-ኦርቶዶክስነት

4ኛ፡-አማራነት ናቸው።

እነዚህን ማንነቶች አሟልቶ በተገኘ ዜጋ ላይ ሁሉም የመከራ ዓይነቶች ተፈጽመውበታል። ይህችን ጦማር በምጽፍባት በዚህች ቅጽበትም እየተፈጸሙበት ነው። አራቱን ማንነቶች ባላሟላው ወገን ላይም በመጠኑም ቢሆን በሰውነቱና በኢትዮጵያዊነት በዘንድሮው ሰሙነ ህማማት በመካሄድ ላይ ካለው መከራ አላመለጠም። ይህንንም የሚክድ ካለ ከወያኔወችና ኦነግ ሸኔወች ጋራ ከመፈረጅ የሚያመልጥ አይመስለኝም።

በዘንድሮው ሰሙነ ህማማት በኢትዮጵያ ምድር ከያለበት እየታደነ የሚታረደው፤ የትኛው ህብረተ ሰብ እንደሆነና፡ ቤቱም የሚያመልክበትም እየተለየ የሚቃጠለው የማን እንደሆነ መግለጽ ከኔ የሚጠበቅ አይመስለኝም።

ይህ ሁሉ መከራና ስቃይ በህዝበ ክርስቲያኑ ላይ በሚካሄድበት በዘንድሮው ሰሙነ ህማማት “የዘንድሮውን ሰሙነ ህማማት ያለበሽታና ያለደዌ ፤ ያለ ድካምና ያለጻእር፤ በደስታ በሰላም እንዳከበርነው፤ የከርሞውንም በተመሳሳዩ ለማክበር ያብቃን“ ማለት እጅግ አያስደንግጥምን? ያለንበትን የመከራና የጭንቅ ሰሙነ ህማማት የመሰለ ዘመን የገጠማቸው ሊቃውንት አበው ምን እያሉ አለፉ?

ካብነት መምህሮቼ እንደሰማሁት፡- የቀደሙ አባቶች ታሪክን ከታሪክ፤ ዘመንን ከዘመን፤ መከራን ከመከራ፤ ትውልድን ከትውልድ ጋራ እያነጻጸሩ በኦርቶዶክሱ ነገረ መለኮት ስልት ልማዶችን እየተረጎሙ፤ ልማዶችን ለገጠሟቸው ችግሮች መፍቻ በማድረግ ኢትዮጵያን፤ ቤተ ክርስቲያናቸውንና ህዝባቸውን ከጥፋት እየተከላከሉ ሀላፊነታቸውን ተወተዋል።

በዘንድሮው ሰሙነ ህማማት የገጠመንን የመሰለ መከራ የቀደሙ አባቶቻችንን በገጠሟቸው ዘመናት “የዘንድሮውን ሰሙነ ህማማት ያለበሽታና ያለደዌ ፤ ያለ ድካምና ያለጻእር፤ በደስታ በሰላም እንዳከበርነው፤ የከርሞውንም በተመሳሳዩ ለማክበር ያብቃን“ እያሉ አላስተወሱትም። ታዲያ ምን እያሉ

አስታወሱት? እንመልከተዋ !

“ከመ ዮም ” (እንደ ዘንድሮው) የምትለውን ከሁለት ቃላት በመጣምር አነጻጻሪ ሆና የምታገለግለውን ቃል በ ዘዮም ተከተው “እንበለ ጻማ ወድካም ዘዮም። ወዘእንበለ ደዌ ወህማም ዘዮም ። ያብጽሀነ ያብጽህክሙ ኀበ ዓም በፍስሀ ወበሰላም” በማለት አስበው ያልፉታል ሲባል ሰምቻለሁ።

“ከመ ዮም ” የምትለው ቃል ስትመዘዝ የከርሞውን ሰሙነ ህማማት በተረጋጋ በሰላም በደስታ ለማክበር ያብቃን“ ማለት ይሆናል። ይህች አፈንጋጭ ቃል ሳትስተካከል በደስታና በሀሴት ለማስታወስ ያብቃን ማለትስ በክርስቶስ ላይ የደረሰውን መከራ መርሳት አይሆንምን ። የሚል ጥያቄ ያስነሳልል። ተነስቷልም። ይላሉ።

ክርስቶስ በመለኮቱ ከሰማየ ሰማያት ወደ ምድር ወርዶ ከድንግል ማርያም በሥጋ ተወልዶ የፈጸመው ሁሉ በምድር ላለው ደቂቀ ዓዳም እንጅ ለራሱ አይደለም። በምድር ላይ የሚሰቃየውን ሰው ለመታደግ ያደረጋችሁት ሁሉ ለኔ እንዳደረጋችሁት ቁጠሩ ነው ያለውን መነሻ በማድረግ፤ ሰወች በሰውነታቸው

ይልቁንም በእምነታቸው ብቻ እየተመረጡ ለመከራ ሲዳረጉ፤ በኦርቶዶክስ እምነታችን መርሆ  በልማድ የሚደረጉትንና የሚባሉትን ለጥብቅናና ለመከላከያ የማይጠቀም የማይመሰክር ቄስ ወይም መምህር የክርስቶስ ጠላት የተረገመና የዲያብሎስ ሠራዊት ነው ይባላል።

"የተጠራችሁለት ለዚህ ነውና ክርስቶስ ፍለጋውን እንድትከተሉ ምሳሌ ትቶላችኋል" ብሎ  ጴጥሮስ እንደነገረን ፩ኛ ጴጥ 2፡21 ፤ ልማዶችን በራሳችን ጉዳት እንዳይደርስብን መጋረጃና መከበሪያ ከማድረግ  አታላይና አስመሳይ ሽፍጥ  አላቀን ለህዝቡ በሚጠቅም መንገድ እንድንተረጉማቸው የክርስቶስን መንገድ ይከተሉ የነበሩት ቀደሙ አባቶቻችን በብዙ ምሳሌወች አስተምረውን ነበር።

ዳዊት በሰላምና በተረጋጋ ዘመን  ሊያደርገው የማይፈቀድለትን በተቸገረ ጊዜ ከመከራ መውጫ በማድረግ መስዋዕቱን እንደተጠቀመበት ክርስቶስ ከታሪክ ጠቅሶ ያስተማረውን  （ማቴ ፲፪፡ 3__5）እኛም በሰላምና በተረጋ ዘመን መደረግ የሌለባቸውን ሁሉ ልማዶች ወደ ራስ ግላዊ ጥቅም ከማዋል ተጠብቀን ወደ ህዝባዊ ጥቅም እንድናሻግራቸው አደራ ብለውን ነበር። በዚህ ዘመን መምህርነቱን ክህነቱን  በገንዘብ እየገዙ የተሰለፉት በመብዛታቸው የነበረውን ባህልና ልማድ ኢትዮጵያን ቤተ ክርስቲያናችንና ህዝባችን ልንታደግባቸው ይቅርና ህዝቡ እስኪነቃ ድረስ ለቤተ ክርስቲያን እውነተኛ ልጆች መጥፊያቸው እየሆኑ ናቸው።  የቤተ ክርስቲያናችንን ብሂል በጥልቅ ሳይረዱ የባህል ጠባቂ የሆኑ ሰወች አውደ ምህረቱን ተቆጣጠረው በተማሩት ልጆቿ ላይ እየዘመቱባቸው ነው።

ክርስቶስም ሀዋርያትም ሊቃውንትም ያደረጓቸው ሁሉ የሰው ልጆች ከገጠሟቸው ችግር መውጫ እያደረጉ እንዲጠቀሙባቸው እንጅ ለልማድ ብለው አንዳች አላደረጉም። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በህማማቱ ሰሞን ካደረጋቸው አንዱን የሀዋርያትን እግር ያጠበበትን እኛም በልማድ የምናደርገውን እንመልከት።

ክርስቶስ እግር ማጠቡ ልማድ ለማድረስ አልነበረም።  ከህጽበተ እግሩ ጋራ በዜማ"ሐዋርያቲሁ ከበበ እግረ አርዳኢሁ ሀጸበ ኮኖሙ አበ ወእመ ወመሀሮሙ ጥበበ" የሚባለው አረፍተ ነገር በህጽበተ እግሩ ውስጥ ያለውን ዋና ቁም ነገር ነገር አካቶታል። ማለትም፡- ክርስቶስ ለሀዋርያት እንደ አባትና እንደ እናት በመሆን እግራቸውን  በማጠብ በናት አባትና በልጅ መካከል ያለውን ጥበብ አስተማራቸው የሚል ነው።

በናት አባትና በልጅ መካከል ያለው ጥበብ ምንድነው?ክርሶቶስ መለኮታዊ ልዕልናውን ከእግራቸው በታች አድርጎ የሐዋርያትን እግር ሲያጥብ እናንተም እንዲህ አድርጉ ያለው፤ በህዝብ ላይ ጉዳት የሚያስከትል ነገር ሲከሰት አስወግዱ ለማለት እንጅ፤ አቧራ ለማራገፍ ወይም እድፍ ለማስወገድ አልነበረም።

እናንተም በህዝቡ ላይ የሚደርሰውን መከራ ችግር ሳትሸሹ ወይም ሳትጸየፉ ክብራችሁን ማእረጋችሁን እርግፍ አርዳችሁ በመተው ወገባችሁን ታጥቃችሁ በህዝቡ ላይ የሚጫነውን መከራ ለማስወገድ ታገሉ ለማለት ነበር።

ጥበብ ማለት “ከመ ንፍታህ ዘኢይትፈታህ” እያልን በየእለቱ የምንደግመው ኪዳኑ እንደሚነግረን እንዳይፈቱ እያደረጉ ሸፍጠኞች በህዝብ ላይ የሚቐጠሯቸውን አዳዲስ የመከራ ገመዶችን እንፈታባቸው ዘንድ መንገድ እንዲያሳዩን ከተሰሩልን ልማዶች ውጭ ሌላ ሊሆኑ አይችሉም።

ወያኔወችና አነግ ሸኔወች በህዝቡ ላይ የሚያነዱት መከራ ወደ መንበረ ጵጵስናችን ወይም ደብራችን እየቀረበ ሲመጣብን፤ ህዝቡን እየጣልን በመሸሻችን መከራው አልደረሰብንም። ስላልደሰብንም “ዘንድሮ ከገጠመን በሽታ ደዌ ስቃይ መከራ ስደት ሞት ተላቀን፤ የከርሞውን በዓል በተረጋጋ በሰላም በደስታ ለማክበር ያብቃን“ የሚለው ልማዳዊ ብሂል ስለራሳችን እንጅ ከህዝቡ ሁኔታ ጋራ ስለተቃረነብኝ ህዝቡን መካድ ሆኖ ተረድቸዋለሁ።

ከህዝቡ እየሸሸን በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ተደበቀን የጸሎት ሐሙስ እለት የእርስ በርሳችንን እግር መተጣጠብ ክርስቶስ እንዲህ አድርጎ ነበር እያልን ችግር የማይፈታ ድራማ ለህዝብ ማሳየት መሰሎ ታየኝ።

ክርስቶስም ሀዋርያትም ሊቃውንት አበው ያደረጓቸው ሁሉ ተደጋግመው መደረጋቸው ልማድ ቢመስሉም ለሰው ህልውና አስፈላጊወች ናቸው። ልማድነታቸው ባይደረግ ይረሳሉ። ከተረሱ በውስጣቸው ያለው ህይወት ጠባቂነታቸው ይቀራል። ህይወት ጠባቂነታቸው ከሌለና ልማድ ብቻ ከሆኑም በልማድነታቸው ብቻ ሊጠበቁና ሊከበሩ አይገባም። ባይደረጉ ቢቀሩ ያሚያጎድሉት ነገር የለምና።

ዛሬ ልማድ የሚመስሉ ነገሮች የተጀመሩት በክፉ ወቅት ለክፉ ችግር መፍቻ ሆነው ነው። ህዝብን አዲስ ችግር ሲገጥመው የነበረው ልማድ ከችግሩ የማያልቅቀው ከሆነ ከንቱ ነው። የሰው ልጅ እግዚአብሄር የሰጠውን አዕምሮ

በመጠቀም የነበረውን ልማድ ሳያቆም ዘመኑ በሚጠይቀው ፈሊጥ አድሶ እየተረጎመ የገጠመውን አዲሱን ችግር ሊፈታበት ይገባል። ልማዱን ሳያቆም ለሰው ልጅ በሚጠቅም መንገድ ቢያደርገው፤ የሰንበት ተማሪወች እንደሚሉት ቅድስናው አይረከስም። ክርስቶስ ስለሚፈልቅበት እንዲያም የበለጠ ይቀደሳል እንጅ።

በቤተ ክርስቲያናችን ሲደረጉ የምናያቸው ሁሉ በልማድ ለልማድ የመጡ አይደሉም። ለምሳሌ ልብስ መልበስ ምግብ መብላት ተደጋግመው በመደረጋቸው ልማድ ናቸው። ልማድነታቸው ቢቀርና ባይደረጉ በህልውናችን ላይ የሚያስከትሉት ጉዳት ሞት ነው። በመደጋገማቸው ልማዶች ናቸው። ትልቁና ዋናው ጥበብ በድግሞሾቻቸው በሰውነታችን የሚያከናውኑት ህይወት ቀጣይነታቸው ነው።

በየዕለቱና በየሰአቱ በልማድ በመደረጋቸው  የምንመገባቸውና የምንለብሰው ልማዶች ቢሆኑም፤ የምንበላቸው ስለልማድነታቸውና ልማድነታቸውን ለማድረስ ብቻ አይደለም። ከልማድነታቸው ባሻገር በሰውነት ላይ ስለሚፈጽሙት ክዋኔወቻቸው ነው።

ቅዱስ ያዕቆብ “ከተግባር የራቀ እምነት የሞተ ነው”  እንዳለው  ለፈጻሚው ህብረተ ሰብ በውስጣቸው ጠቃሚ ክንውኖች ከሌሉባቸው በየዓመቱም ሆነ በየእለቱ የሚደረጉ ልማዶች ሁሉ የሞቱ ናቸው።

በክርስቶስ በሐዋርያትና በሊቃውንት ባንድ ወቅት ለህዝብ በሚጠቅም መንገድ የተደረጉትን  ደጋግመን የምንፈጽማቸው ውርሶች፤ ከተግባር ካራቅናቸው ከቤዘነታቸው አላቀን የህዝብ ማደንዘዣና ማፍዘዣ ማድረጋችንን መርሳት የለብንም።

በቅርቡ የኮረናው  ክስተት ያስከተለው ውዝግብ በቂ ትምህርት የሚሰጠን ይመስለኛል። የበሽታው ትልቁና ዋናው መከላከያ መራራቅና አለመነካካት ከቤት ወጥተን በጋባን ቁጥር እጅን መታጠብ እንደሆነ ተረጋግጧል። ይህም በተለምዶ በምናደርጋቸው ማህበራውያን ይዘቶች ላይ፤ በተለይም የቀደሙ ነገሮችን አጥብቃ በመያዝ ደጋግማ በማታደርገው በኛ ቤተ ክርስቲያን ላይ ከባድ ተጽእኖ አሳድሯል።

በደህና ጊዜ ቅዱስ ቁርባኑን የምንሳተፍባት አንዲት ማንኪያ  (እርፈ መስቀል ) ነበረች።  ባንዲት ማንኪያ የምንፈጽመው ተሳትፎ ኮረናውን ለመከላከል

እንድናደርጋቸው ከመከሩን ምክር ጋራ የሚቃረን ነው። ቁርባኑ ይቅር? ወይስ የምንሳተፍባት ማንኪያ ትቅር? የሚል ውዝግብና ጭቅጭቅ አስከትሏል።

ህዝብ በልማድ አዘውትሮ የሚያየውና የሚያውቀው ከፊቱ ሲወገድ ብቻ ይጠይቃል። ታሪክ እየጠቀሰና ኩነቶችን እያገናዘበ ሳያስረዳ በኃይልና በእልክ ለመለወጥ የሚሞክረውን ህዝብ አምባ ገነን መናፍቅ ቢለው አይፈረድበትም። ነገር ግን ከታሪክ ተጠቅሶ ሳይዛባና ሳይሸፈን እንዲረዳው ሆኖ ከቀረበለት ህዝብ ለራሱ ሲል ይቀበለዋል። ቁርባኑንም ከበፊቱ በላቀና በበለጠ ግንዛቤ ያከብረዋል።

ነገር ግን "ካባቶቻችን የተቀበልነው ውርስ ነውና ማንኪያው መቀየር የለበትም" ብሎ ለማንኪያው ጥብቅና የሚቆም ካለ የክርስቶስ ተልእኮ ያልገባው በክርስቶስ የተጀመረው ያንድ ጽዋዕ ተሳትፎ ባንዲት ማንኪያ መተካቱን ያላወቀና ራሷ ማንኪያዋ ለምንና መቼ ማን እንደከተታት ያልተረዳ ሰው ነው። እኔ በማገለግልበት በከንሳስ መድኃኔዓለም ምእመናን ጥያቄው ተነስቷል።

በዘመናችን ለሚነሳው ጥያቄ መመለስ የሚችል ሲኖዶስ ባለመኖሩ፤ የነበረን አማራጭ ክርስቶስ "የዘላለም ህይወት ያላቸው የሚመስሏችሁን መጻህፍትን መርምሩ ስለኔ ይመሰክራሉ ህይወት እንዲሆንላችሁ ወደ ልትመጡ አትወዱም" ዮሐን 5፡39) ያለውን በመከተል ሊቃውንት አበው የሰሩልንንና ያደረጉትን ፈለግ ሳንለቅ ችግራችንን ፈተናል።

በልማድ መልክ ሲካሄዱ የኖሩት የተጀምሩት በችግር ነው። በሰላምና በተረጋጋ ዘመን መሰረታዊ ህልውናቸው ሳይናጋ ይደረጋሉ እንጅ አይታጎሉም። ዘመኑ ክፍቶ ህዝብ ከችግር ላይ ሲወድቅ አጠቃቀማቸውን በመቀየር ችግሩን ለመፍታት ወደሚያስችሉፈበት መንገድ በመቀየር ችግሩን ይፈቱባትል እንጅ አይታጎሉም።

ክርስቶስ የጀመረው የአንድ ጽዋዕ ተሳትፎ እስከ ሶስተኛው ክፍለ ዘመን ቀጥሎ ፤ በዘመነ ሊቃውንት ችግር ተከሰተ። የተከሰተው ችግር አዲስ ስርአት አስከተለ። ይህም አዲስ ስርአት ማንኪያ መጠቀም ነበር።

ማንኪያዋን መጠቀም እንዲከሰት ያደረገው ችግር፤ ስልጣን ያላቸው ሰዎችና ታይታን የሚወዱ ሰዎች የፊት ወንበሩን በመያዛቸው ጽዋውን ሲቀባበሉ ወይኑ ያልቅና ለታይታ ግድ የሌላቸው ሰወች ወደኋላ ስለሚቀመጡ ወይኑ ሳይደርሳቸው ያልቃል። በዘመኑ የነበሩት አባቶች ለሁሉም እንዲዳደረስ ለማድረግ ማንኪያዋን

እንደተጠቀሙ መምህሮቼ ሲነገሩ ሰምቻለሁ። ማንኪዋን የችግራቸው መፍቻ አደረጌት። ከዚያ ዘመን ጀምሮ ኮረና እስኪሰት ድረስ ማንኪዋ ስታገለግል ኖራለች። በኛ ዘመን ደግሞ የኮረና መከሰት በማንኪዋ ላይ ጥያቄ አስንስቷል። በከንሳስ መድኃኔ ዓለም ማህበረ ምእመናን መካከል ጥያቄው ተነስቶ  ልማዱን ሳንተው ክርስቶስ ያስተማረውን ሀዋርያት የተከተሉትን ሊቃውንት አበው የሄዱበትን ፈለግ በመከተል ከመከፋፈል ከጭቅጭቅ ውስጥ ሳንገባ ችግሩን ፈተነዋል።

የነበረው ባህል ለራስ ክብርና ጥቅም ከለላ ሳናደርግ፤ በድፍረትና በግምት ለመቀየር ከመሞከርም በመራቅ፤ የቆዩትን ባህሎች ሳይንቁና ሳይለቁ ለሰው በሚጠቅሙ ፈሊጦች የሚደረጉ ሁሉ ከእግዚአንሄር ፈቃድና ከባህሉ ይዘቶች ጋራ አይጋጩም። ከሰው በለይ የሚከበር ቁስ የለምና ። "እግዚአብሔር ከሰው ውጭ የሆኑትን ፍጥረታትን ሲፈጥር በራሱ አምሳል ሳይሆን በየወገናቸው ነው። ሰውን ሲፈጥር ግን በራሱ አምሳል ከራሱ ጋራ ወገንተኛ በማድረግ ነው። ክርስቶስ አምሳሉና ወገኑ የሆነውን  ሰው ከገባበት ችግር ለማውጣት ወደ መሬት ወርዶ ሲያድን "እኔ የማደርገውን ታደርጋላችህ። እኔ ካደረኩትም የበለጠ ታደርጋላችሁ" እንዳለው፤ ሰው ከግለኝነት ተላቆ  ራሱን ከማምለክ ርቆ፤ ራሱን ዝቅ አድርጎ የእግዚአብሔርን ፍጥረታት የሚያነብ ከሆነና የፍጥረታትንን ባለቤት ፈቃድ የሚከተል ከሆነ  መፍታት የማይችለው ችግር አይገጥመውም" ይላሉ አባቶች።

በሰው ላይ የሚደርስ ግፍና መከራ በእግዚአብሄር ላይ እንደደረሰ የሚቆጠረውና ለሰው የሚደረገው መልካም ውለታም በእግዚአብሀር የሚያስመሰግነው፤  ባያደርገው ግን የሚያስወቅሰው በዚሁ ምክንያት ነው።

ጎርጎርዮስ የሚባለው ሊቅ "ንዑ ትርአዩ ዘንተ ቅስፈተ"  (ጎር ቁ 40__45) ብሎ የተናገረውን ሊቃውንት በትርጌሚያቸው እንዳስተማሩን ዛሬ በሀገራችን እንደሚደረገው የሰውን ክቡር ሰውነት የሚደመስስ ግፈኛ ሲከሰት በሩቅና በቅርብ ላለ ሰው ለማሰማት የጥሪ ድምጽ እንደሆነ ነው ።  "ገአረ ኢየሱስ ኀበ አቡሁ። . . . . ወሀበ አዳም ገብሩ  ( ሰለስት 96፣ 99) ። የሚለው ምንባብም የሚያስተምረን፡- በክርስቲያኖች ላይ የሚደርሰው መከራ እንዳይሸፈን  ክርስቶስ በመስቀል ላይ በደረሰበት መከራ አማካይነት ለደቂቀ አዳም በተግባር ለማሳየትና በድምጽም ለመመስከር የሚረዳ ልማድ ነው።

ንባቡ እንደሚያመለክተው ክርስቶስ ከሰማየ ሰማያት ወርዶ  ለባህርይ አባቱና በምድር ላለው ለደቂቀ አዳም በመስቀል ላይ ያሰማው ድምጽ በሰው ላይ በሚፈጸመው ግፍና መከራ ክስና ይግባኝ እንጅ በራሱ ላይ በመፈጸሙ ለራሱ ያደረገው አይደለም። ለራሳችሁ እንጅ ለኔ አልቅሱ እዘኑ አላለም።

በምድር ላይ የሚሰቃየውን ሰው ለመታደግ ያደረጋችሁት ሁሉ ለኔ እንዳደረጋችሁት ቁጠሩ።   ከሁሉ ለሚያንሱ ላንዱ ስላለደራችሁት ለኔ አላደራችሁትም ርጉማን ለሰይጣን ለሰራዊቱ  ወደተዘጋጀው ወደ ዘላለም እሳት ሂዱ“ ያለው ቃል የሚያዘናጋ አይደለም።  ማቴ 25፡ 40__41)።

ቅዱስ ጳውሎስ በሮሜ 8፡17 ላይ በሰፈረው ትምህርቱ የህዝበ ክርስቲያኑን መከራ ባለመካፈላችን የፍርሀትና የራሳችን ሥጋዊ ፍላጎት አገልጋዮች እንጅ የእግዚአብሄር ልጆች መሆን አለመቻላችን ገልጾልናል።  የእግዚአብሔር ልጆች

1ኛ፡-በኢትዮጵያዊነታቸው

2ኛ፡-በኦርቶዶክስነታቸው

3ኛ፡-ባማራነታቸው

4ኛ፡-በሰውነታቸው  እየተመረጡ በሚታረዱበት፤ የኦርቶዶክስ

አብያተ ክርስቲያናት በሚቃጠሉበት በዘንድሮው ሰሙነ ህማማት ፓትርያርኩ የገባቸውና የተሰማቸው ቢሆኑ፤  በክርስቶስ ስቅለት አማካይነት  የህዝቡን ስቅላት ለደቂቀ አዳም አንድ ላይ ሆነን ኑ እናሰማ ብለው የአዲስ አበባ አድባራትን በመጥራት የህዝቡን መከራና ስቃይ በመስቀል አደባይ ለዓለም ማሰማት ይችሉ ነበር።   የቀሩት ጳጳሳትም የሳቸውን ፈለግ በመከተል፤ በየሀገረ ስብከታቸው ካሉት አብያተ ክርስቲያናት ጋራ  በተሰቀለው በክርስቶስ አካል አማካይነት በመቃጠል በመታረድና በመጨፍጨፍ ላይ ያለውን የህዝቡን ስቃይ በየከተሞቻቸው ለደቂቀ አዳም እንዲያሳዩ ተጽእኖ ያሳድሩባቸው ነበር።

ከዚህ ግንዛቤ ላይ መድረሳቸው ይቅርና የነበሩት ልማዶችን መረዳት ስለተሳናቸው “የዘንድሮውን ሰሙነ ህማማት ያለበሽታና ያለደዌ ፤ ያለ ድካምና ያለጻእር፤ በደስታ በሰላም እንዳስታወስነው ፤ የከርሞውንም በተመሳሳዩ  ለማሰብ ያብቃን“ በማለት አሳለፉት።

በመከራ ዘመን ሰሙነ ህማማቱን ያሳለፉት አባቶች እንዴት እንዳሳለፉት ሲነገር የሰማሁትን ደብቄና አፍኜ መያዜ፤ መንፈሳቸው ወቀሰኝ። መከራውና ስቃዩ አሁንም ይቀጥል ማለትም ስለመሰለኝ ከህሊና ወቀሳ ራሴን ለማዳን ይህችን ጦማር ለማቅረብ ተገደድኩ። እግዚአብሔር ከዘንድሮው መከራ አላቆ የከርሞውን ሰሙነ ህማማት በተረጋጋና በደስታ ለማስታወስ ያብቃን !

ይቆየን !